የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Regional Integration

# የቁም እንስሳት ኤክስፖርት ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 863/2014

ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

ታህሳስ/2014 ዓ.ም

# <u>የቁም እንስሳት ኤክስፖርት ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ ለመወሰን የወጣ መመሪያ</u>

# <u>ቁጥር 863/2014</u>

ለውጪ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት ሀገራዊ ጥቅምን ለማስከበር እንዲቻልና በመስኩ እየታየ የሚገኘውን ከዋጋ በታች አሳንሶ በመሸጥ የውጭ ምንዛሪ ግኝታችንን ማሳጣት እና በመስኩ የኮንትሮባንድ ንግድ እተስፋፋ መምጣትን መግታት በማስፈለጉ፤

ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ መመሪያ የመሸጫ ዋጋን የተከተለ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ግብይቱን በመከታተልና መቆጣጠር የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት ላኪዎች የእንስሳት የግብይት ዋጋ ወቅታዊና ተዓማኒ መረጃዎች እንዲኖራቸው ማድረግ በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ቁጥር 819/2006 አንቀጽ 18 (2) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ፤

ይህ መመርያ ‹‹የቁም እንስሳት ኤክስፖርት ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 863/2014ዓ.ም›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ፤

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፤

1. “አዋጅ” ማለት የቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ቁጥር 819/2006 ነው ፡፡
2. “ደንብ” ማለት የቁም እንስሳት ግብይት ደንብ ቁጥር 341/2007 ነው፡፡

3. “መመሪያ” ማለት የቁም እንስሳት ግብይትን ስርዓት አፈጻጸም ለመተግበር ከዚህ ቀደም ብሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 004/2007 ሲሆን፤ የቁም እንስሳት ኤክስፖርት አነስተኛ የመሸጫ ዋጋ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 863/2014 ያካትታል፡፡

4. “የቁም እንስሳት” ማለት የዳልጋ ከብትን፣ በግን፣ ፍየልን፣ ግመልን እና ሚኒስቴሩ የቁም እንስሳ ብሎ የሚሰይማቸውን ሌሎች እንስሳት ይጨምራል፤

5. “የቁም እንስሳት ግብይት” ማለት የቁም እንስሳት ሽያጭን፣ ግዢን፣ ማጓጓዝን፣ የእንስሳት ማድለቢያ ማከራይትን እና ሌሎች ተመሳሳይ የግብይት ተግባራትን የሚያካትት ሂደት ነው፤

6. “የመጀመሪያ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል” ማለት አግባብ ባለው አካል የተሰየመና በዚህ አዋጅ መሠረት የቁም እንስሳት ግብይት የሚከናወንበት ቦታ ነው፤

7. “ላኪ” ማለት የቁም እንስሳትን ወይም ሥጋንና የሥጋ ውጤቶችን ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ነው፤

8. “ድርድር” ማለት በሻጭና በገዢ መካከል በቀጥታ በሚካሄድ ክርክር አማካይነት የቁም እንስሳት ዋጋ የሚወሰንበትና የባለቤትነት ዝውውር የሚፈጸምበት የግብይት ሥርዓት ነው፤

9. “የኳራንቲን ጣቢያ” ማለት የቁም እንስሳትን በተከለለ ስፍራ ለተወሰነ ጊዜ ከሌሎች እንስሳት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንዳይገናኙ በማድረግ ጤንነታቸውን ለመከታተል እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ የክትባት ወይም የህክምና አገልግሎት

10. “አግባብ ያለው አካል” ማለት እንደ አግባቡ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴሩ ወይም በክልል የቁም እንስሳት ግብይትን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ነው፤

11. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

12. “እንደውል ያለመፈጸም” ማለት ላኪው ከገዥው ጋር በገባው ውል መሰረት ለመፈፀም የማይችልበት ማናቸውም ምክንያቶች ሲሆኑ የዋጋ ለውጥን አያካትትም፡፡

13. “የዋጋ ማነጻጸሪያ ቦርድ” ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት በየሳምንቱ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳትን የመላኪያ ዋጋ የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም የሚያዘጋጅ አካል ነው፡፡

14. “የዋጋ ማነፃፀሪያ” ማለት ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳትን የመላኪያ ዋጋ በዝርያ፤ መጠን እና ሌሎች ለጉዳዩ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን በማሰባሰብና በመተንተን በቦርዱ በየወሩ የሚዘጋጅ የመላኪያ ዋጋ ማነፃፀሪያ ነው፡፡

15. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸ ሴትንም ይጨምራል፡፡

3. **የተፈጻሚነት ወሰን፤**

ይህ መመሪያ በአገሪቱ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በወጪ የቁም እንስሳት ግብይት ላይ በሚሳተፍ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የቁም እንስሳት ኤክስፖርት ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ ለመወሰን የመረጃ ምንጮች፤

4. **ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት አነስተኛ ዋጋ ለማውጣት በግብዓትነት የሚጠቀምባቸው የመረጃ ምንጮችና የአሰራር ስሌት፤**

1. በሀገር ውስጥ ከብሔራዊ የቁም እንስሳት የገበያ መረጃ ስርዓት ከተመረጡ የቁም እንስሳት የገበያ ማዕከላት በየወሩ ከተሰበሰበው የሀገር ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የመሸጫ ዋጋ፣
2. የዓለም አቀፍ ንግድ ማዕከል የሚገኝ የቁም እንስሳት የየእለቱና የወሩ ሽያጭ አማካይ በማውጣት፡፡
3. ከግምሩክ ኮሚሽን በሚገኝ የቁም እንስሳት የተመዘገበ የመላኪያ ዋጋ፤

4. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት አነስተኛ ዋጋ ለማውጣት ከየሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች የተመረጡ የኮሚቴ አባላት ከላይ ከቁጥር 1-3 በተገለጹት የመረጃ ምንጮችና የተሻለ የመረጃ ምንጮች ሲገኙ በመጠቀም፣ በመደመር፣ በማካፈልና አማካይ ውጤት በመውሰድ የቀረበ ነው፡፡

**5. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት አነስተኛ ዋጋ ለማውጣት አዘጋጅ የኮሚቴ አባላት፤**

ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት አነስተኛ ዋጋ ለማውጣት የሚያዘጋጅ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴር ዲኤታ የሆነ የኮሚቴ ቦርድ በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፡፡

1. የንግድ ትስስርና የወጪ ንግድ ዘርፍ ሚኒስቴር ዲኤታ-----------------------------ሠብሳቢ
2. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ --------------------------------------------------------------አባል
3. የግብርና ሚኒስቴር ----------------------------------------------------------------------አባል
4. የገቢዎች ሚኒስቴር ----------------------------------------------------------------------አባል
5. የጉምሩክ ኮሚሽን -----------------------------------------------------------------------አባል
6. የኢትዮጵያ የቁም እንስሳት ላኪዎች ማህበር -----------------------------------------አባል
7. የኢትዮጵያ የቁም እንስሳት ነጋዴዎች ማህበር ---------------------------------------አባል
8. የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የቁም እንስሳት ግብይት ዳ/ት ---------------- አባልና ፀኃፊ ሲሆኑ በየወሩ እየተገናኙ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ ለውሳኔ ያቀርባሉ፤ ተወስኖ ሲጸድቅ ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የተቋማት ኃላፊነት

6. የንግድ ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ተግባራትና ኃላፊነት፤

   1. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት የመሸጫ ዋጋ ማነጻጸሪያ ወቅቱን ጠብቆ እንዲዘጋጅ ያስተባብራል፤
   2. በወሩ የቁም እንስሳትን ለውጭ ገበያ ዋጋ አሳንሶ የሸጠ ወይም ሽጫለሁ ብሎ ያስመዘገበ ተብለው የተለዩ እና በብሔራዊ ባንክ እርምጃ በተወሰደባቸው ላኪዎች ላይ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፣
   3. በቦርዱ የተዘጋጁ ዋጋ ማነጻጸሪያዎችን በየወሩ ለብሔራዊ ባንክ እንዲደርስ ያደርጋል፣
   4. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት አሰራርን፣ የተላኩ የገበያ መዳረሻ በታች ጥናት ያከናውናል ፣ሲፈቀድም ያስተባብራል፤
   5. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳትና የላኪዎችን አስፈላጊ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያደራጃል በማጠናከርም ለተፈለጉበት ዓላማ እንዲውል ያደርጋል፤
   6. መስኩ የሚጠይቀውን የድጋፍ ፣የማበረታቻና የቁጥጥር ስራዎችን ያከናውናል፤
   7. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት ግብይት ላይ እንደውል በማይፈጽሙ ወይም አሳሳች ድርጊት በሚፈጽሙ ወይም የሀገር ገጽታን በሚያጎድፉ አካላት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡
   8. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት የዋጋ ማነጻጸሪያ መረጃዎችን በመሰብሰብ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል፤
   9. በዚህ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ወደ ውጭ የተላኩ የቁም እንስሳት መጠን፤ ቀን፤ ላኪ ተቀባይ /ገገር እና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎችን ይይዛል፣
   10. የዚህን መመርያ አፈጻጸም እና የሚታዩ ክፍተቶችን በመለየት አስፈላጊውን ማስተካከያ ይወስዳል፣

11. የራሱን የአፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት የባለድርሻ አካላት የምክክር የስብሰባ መድረክ ያዘጋጃል፣ ለስብሰባው አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ይህንን መመሪያ ያስፈጽማል፡፡

7. የግብርና ሚኒስቴር ተግባራትና ኃላፊነት፤

1. ለውጪ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳትን ጤና በመመርመር የጤና መስፈርት ላሟሉት የቁም እንስሳትን የእንሰሳት ጤና ምስክር ወረቀት ለላኪው ይሰጣል፣
2. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳቱ የተሟላ መረጃ ሰነዶች መኖራቸውን ያረጋግጣል፤
3. የዋጋ ማነጻጻሪያ ዝግጅት ላይ የሚሳተፍ ብቁ ከፍተኛ ባለሙያ ወይም የስራ ኃላፊ ይመድባል፤
4. ለውጪ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት የግብይት ስርዓት ለማሻሻል የሚረዱ ጠቃሚ ሀሳቦችን ያመነጫል ተቀናጅቶም ይሰራል፡፡
5. በሚዘጋጀውና በሚጠራው የባለድርሻ አካላት የምክክር ስብሰባ ላይ የራሱን የአፈጻጸም ሪፖርት ይዞ ይቀርባል፡፡

8. የጉምሩክ ኮሚሽን ተግባራትና ኃላፊነት፤

1. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት መረጃዎችንና ሰነዶች በማጣራት እና በማረጋገጥ በወቅቱ እንዲልኩ ይተባበራል፣
2. ወደ ውጭ የተላኩ የቁም እንስሳት መጠን፤ ቀን፤ ላኪ፤ ተቀባይ/ ገዢ እና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎችን ተደራሽ በሆነ መንገድ በመገናኛ ዘዴ ይልካል፤
3. የዋጋ ማነጻጻሪያ ዝግጅት ላይ የሚሳተፍ ብቁ ከፍተኛ ባለሙያ ወይም የስራ ኃላፊ ይመድባል፡፡
4. በሚዘጋጀውና በሚጠራው የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረክ ላይ የራሱን የአፈጻጸም ሪፖርት ይዞ ይቀርባል፡፡

9. **የብሔራዊ ባንክ ተግባራት፤**

1. ወቅታዊ መረጃን መሠረት በማድረግ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳትን የመላኪያ ዋጋ መሠረት መከናወኑን ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ያሳውቃል፤
2. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳትን የመላኪያ ዋጋን ተቀናጅቶ በመስራት መረጃ ይሰጣል፤
3. የዋጋ ማነጻጸሪያ ዝግጅት ላይ የሚሳተፍ ብቁ ከፍተኛ ባለሙያ ወይም የስራ ኃላፊ ይመድባል፤
4. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት የመላኪያ ዋጋ መረጃዎች እና ሌሎችም ለመላክ ጠቃሚ መረጃዎችን ለሚመለከታቸው ሁሉ ተደራሽ በሆነ የመገናኛ ዘዴ ያደርሳል፤
5. በሚዘጋጀውና በሚጠራው የባለድርሻ አካላት የምክክር ስብሰባ ላይ የራሱን የአፈጻጸም ሪፖርት ይዞ ይቀርባል፡፡

10. **የቁም እንስሳት ላኪዎች ማህበር ተግባርና ኃላፊነት፤**

1. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት ዋጋ ማነጻጸሪያ ዝግጅት ላይ የሚሳተፍ ሁለት በመስኩ ብቃት ያላቸው አባላትን ይመድባል፤
2. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት የዋጋ ማነጻጸሪያ ዝግጅት ላይ በንቃት ይሳተፋል፣ መረጃዎችንም ለአባላቱ እና ግብይት ለሚካሄድባቸው ቦታዎች በወቅቱ ተደራሽ በሆነ የግንኙነት ዘዴ ያደርሳል፣ግብረመልሶችንም በማጠናከር ለሚመለከታቸው ሁሉ ሪፖርት ያቀርባል፤
3. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት ግብይትን በተመለከተ ለመስኩ ጠቃሚ የሆኑ ማናቸውንም ተግባራት ያከናውናል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋርም በትብብር ይሰራል፤
4. የዋጋ ማነጻጸሪያ ዝግጅት ላይ የሚሳተፍ ብቁ ከፍተኛ ባለሙያ ወይም የስራ ኃላፊ ይመድባል፤

5. በሚዘጋጀውና በሚጠራው የባለድርሻ አካላት የምክክር ስብሰባ ላይ የራሱን የአፈጻጸም ሪፖርት ይዞ ይቀርባል፡፡

11. **የላኪ ኃላፊነት/ ግዴታ፤**

1. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት መላኪያ ዋጋን ይከታተላል ይተገብራል፤
2. የቁም እንስሳትን ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ማንኛውም ላኪ የሚያቀርባቸው እያንዳንዱ የባንክ ሠነዶች ማለትም ፕሮፎርማ ኢንቮይስ፣ የውል ስምምነት፣ ሌተር ኦፍ ክሬዲት፣ የባንክ ፈቃድ እና ለግብይቱ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ማናቸውንም ሠነዶች ያደራጃል ለሚመለከተውም ያቀርባል፡፡
3. የቁም እንስሳት ክብደትን፣ የምርት አገር /ቦታ፣ የተገዛበት የግብይት ማዕከልን የኳራንቲን የምስክር ወረቀቶችንና ሌሎችን አግባብ ያለው አካል የሚጠይቃቸውን መረጃዎች የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡
4. የቁም እንስሰሳት ላኪዎች የገዟቸውን የቁም እንስሳት ጤንነትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፤
5. ከውጭ ገገሮች ጋር የገቧቸውን ውሎች ለብሄራዊ ባንክ እና ለሚንስቴር መስሪያቤቱ የማስመዝገብ ግዴታ አለባቸው፡፡
6. በውሉ መሰረት የመከላኪያ ጊዜውንና ሁኔታዎችን ጠብቆ ይልካል፤
7. እንደውል ለመፈጸም የማይችሉበት ሁኔታ ከተከሰተ በአምስት /5/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ለሚንስቴር መ/ቤቱ ወይም ለብሄራዊ ባንክ የማሳወቅ እና የሚሰጠውን አቅጣጫ ይከታተላል፤
8. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት የማቆያ/ማድለቢያ ስፍራዎችን ለሚንስቴር መ/ቤቱ ያሳውቃል፤ለቁጥጥር ስራም ይተባበራል፤
9. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት የዝርያ አይነት፣ ክብደት እና ሌሎች ተያያዥ አሰራሮችን ግብርና ሚኒስቴር ወይም አግባብነት ያለው አካል የሚሰጠውን ውሳኔ የመቀበል ግዴታ አለበት፤
10. የዕለቱን የቁም እንስሳት ግዢና መረጃዎችን፣ ቁም እንስሳት ዝርያ በብዛት እና ዋጋን መዝግቦ የመያዝና አግባብ ያለው አካል ሲጠየቅ መረጃ ይሰጣል፤

11. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳትን ከሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ብቻ የመግዛት ግዴታ አለበት፣

12. የሃገሪቱን ጥቅምና መልካም የንግድ ገጽታ ከሚያጎድፉና ከአሳሳች ተግባራት የመቆጠብ ግዴታ አለበት፤

13. የዋጋ ማነጻጸሪያ ዝግጅት ላይ የሚሳተፍ ብቁ ከፍተኛ ባለሙያ ወይም የስራ ኃላፊ ይመድባል፤

14. በሚዘጋጀውና በሚጠራው የባለድርሻ አካላት የምክክር ስብሰባ ላይ የራሱን የአፈጻጸም ሪፖርት ይዞ ይቀርባል፡፡

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች፤

**12.ስለተሸሩ እና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ በፊት በቁም እንስሳት ኤክስፖርት ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ ለመወሰን የወጡ መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

**13. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከጥር 01/ 2014 ዓ/ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**14. መመሪያውን ስለመሻር ወይም ስለማሻሻል፤**

ይህ መመሪያ ለማሻሻል በሀገር ውስጥና በመሸጫ መዳረሻ ሀገራት የገበያ ጥናት በማድረግ የተሻለ አማራጭ አሰራር ሲኖር እየተሻሻለ የሚቀርብ ሲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህንን መመሪያ ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው ይችላል፡፡

**15. አባሪ 1**

ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በመሆን የተያያዘው ሰንጠረዥ ከጥር 01/ 2014 ዓ.ም እስከ መጋቢት 30/2014 ዓ.ም ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት የመላኪያ ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ገብረ መስቀል ጫላ

የኢ.ፌዲሪ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር

**አባሪ 1. ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ፤**

| ተ.ቁ. | ቁም እንስሳት | ኪሎ ግራም | አማካይ ዋጋ |
|---|---|---|---|
| 1 | ዳልጋ ከብት ወይፈን | ከ320 ኪሎ ግራም እና ከዛ በታች | 650 የአሜሪካን ዶላር |
| 2 | ዳልጋ ከብት ኮርማ | ከ320 ኪሎ ግራም በላይ | 750 የአሜሪካን ዶላር እንዲሸጥ |
| 3 | ግመል | ከ500 ኪሎ ግራም በላይ | 750 የአሜሪካን ዶላር |
| 4 | ግመል | እስከ 500 ኪሎ ግራም | 550 የአሜሪካን ዶላር፤ |
| 5 | በግ ዋንኬ | ከ15-25 ኪሎ ግራም | 75 የአሜሪካን ዶላር፤ |
| 6 | በግ ዋንኬ | ከ25 ኪሎ ግራም በላይ | 85 የአሜሪካን ዶላር፤ |
| 7 | አዳል በግ | 18-23 ኪሎ ግራም | 65 የአሜሪካን ዶላር |
| 8 | አዳል በግ | ከ23 ኪሎ ግራም በላይ | 70 የአሜሪካን ዶላር |
| 9 | ፍየል | ከ20-25 ኪሎ ግራም | 70 የአሜሪካን ዶላር |
| 10 | ፍየል | 25 ኪሎ ግራም በላይ | 80 የአሜሪካን ዶላር |